# <u>የወረወርኩት አንካሴ ተመልሶ በራሴ</u>

*በፀጋዬ ደባልቀው*
*<u>ዋሽንግተን ዲሲ</u>*

በወርሃ ግንቦት 2002 ዓ.ም. ላይ እውን የሚሆነው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ድምጽ እያስገመገመ ለመቃረቡ ምልዓተ ተዋናያኑ ተፍ ተፍ ማለት መጀመራቸው ከ"ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ" ዓይነት አካሄድ ተላቀን ወደ ተረጋጋና አልሞና ሰንቆ ወደመጓዙ እያዘመምን ለመምጣታችን አዎንታዊ መገለጫ ነውና እሰየው ይልመድብን ያስብላል::

ለሃገር ልማትና ሠላም መረጋገጥ፣ ለሕዝብ መብት መከበርና ለቀጣይ ዲሞክራሲያዊና ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት በአስተማማኝነትና በዘላቂነት መታነጽ የሚቀረቀሩና የሚተጉ ወገኖች ባንድ ገጽ ምርጫው ዲሞክራሲያዊ፣ ሰላማዊ፣ ርትዓዊና ነጻ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ከወዲሁ የሚያደርጉት አዎንታዊ እንቅስቃሴ ልብን የሚያደነድነውን ያህል፤ ለኘሮፖጋንዳ ፍጆታ፣ ለመሰሪ ዓላማ ማራመጃና ለ"ባወጣ ያውጣው" የሥልጣን መፈናጠጫ ግብ መምቻ በምርጫ ዋዜማ "እዩኝ እዩኝ" አባዜ የተለከፉ ወገኖች እንደትላንቱ ሁሉ ዛሬም ያዙኝ ልቀቁኝ እያሉ በየአደባባዩ ሲፏልሉና ሽርጉድ ሲሉ ከሩቅም ከቅርብም እየታዘብን ነው:: ትላንት ለሰላማዊ ትግል ከኛ በላይ ላሳር የሚለውን ገራገር ገብስ መፈክር ከፊት ለፊት አንግበው መራጩን ሕዝብ በድምጽህ ይሁንታን ካላበስከን በአንዲት ጀምበር ሁሉ በእጅህ ሁሉ በደጅህ ሆኖ ሕብስተ መና ከሰማይ እናዘንብልሃለን እያሉ በአፈ ጮሌነት ጤፍ በሚቆላው ምላሳቸው እየተንጣጡ ሲሰብኩት፣ እዛው በዛው ደግሞ ቁርሾና ጥላቻን፣ ዘረኝነትን እርስ በእርስ መቦጫጨቅንና መናከስን መራራቅንና ጎራ ለይቶ የመገዳደልን ሴራ ሲደግሱለት እጅ ከፍንጅ ስላገኛቸው አክ እንትፍ ብሎ በመትፋት ከመድረኩ ወጊድ በማለት የልማት፣ የሰላምና የዲሞክራሲ ሂደት ጉዞውን በአርሞሞ ገፍቶበታል::

አሁንም የሰላም ለምድ የለበሱ ሞገደኞችና ጽንፈኞች ከጀርባ ሆነው እንደወትሮው ሁሉ የሕጋዊና ሰላማዊ መፈክር ያነገቡትን ፊት ለፊት በማስቀደም የለመዱትን ጀብደኛ ትንኮሳ፣ ዘረኛ ቅስቀሳና የልብ ወለድ ወቀሳ ጦራቸውን እየሰበቁ የእናቴ ቀሚስ አደናቀፈኝ ሰበብ አስባብ በመደርደር መጪውን ምርጫ ተንተርሰው ከወዲሁ ፖለቲካዊ ሥርዓቱን ቢቻላቸው ለመገዝገዝ አልያም ጥላሸት በመቀባት በዓለም ሕዝብ ዘንድ ከል እንዲላበስ ያለ የሌለ ውስጣዊና ውጭያዊ ኃይላቸውን አስተባብረው በመዝመት ላይ ናቸው::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያን ሕዝብ የልማት ግስጋሴ በጎሪጥ የሚመለከቱና ድህነት ለአንጄና ለሁሌ አቁማዳውን ጠቅልሎ ከምድረ ኢትዮጵያ ገጽታ ይጠፋ ዘንድ ሕዝቡና መንግሥት በእልህ በቁጭትና በጽናት የተያያዙት ርብርቦሽ የማይዋጥላቸው ወገኖች ከተራ አሉባልታ እስከ መሠሪ ቁማታ በመክፈት ያላቸውን የጥፋት ሳንጃ ወድረውብታል::

በሃገር ውስጥ የተጀመረውን ጥረት የሚያጠናክሩ፣ የህግ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እርምጃዎችን ከትክክለኛና ከቆሙለት አይነተኛ ማዕቀፍ ይሁነኝ ብለው ከማጣመም ጀምሮ በውጪው የዲኘሎማሲያዊው ዓለም በሃገራችን ላይ የተዛባ ግንዛቤ እንዲኖረው የማድረጉን እኩይ እንቅስቃሴ አፋፍመውታል::

በሃገር ቤት የሰላማዊ ትግል አጋፋሪና አራማጅ እኛ ብቻ ነን ብለው ራሳቸውን የሾሙት አንዳንድ ኃይሎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተከታታይነት እያሳዩ ያሉት የትግል ባህርይ የ"እኔን" ምረጡ የአዘቦት ቀን አካሄድ ነው ብሎ ደምድሞ መቀመጥ ካለፈው ምርጫ ሂደትና ውጤት ሁነኛ ትምህርት

ያለመውሰድ ፖለቲካዊ የዋህነት የሚወልደው ክስተት ብቻ ነው። በተለይም ወጣቱና የነገይቱ ኢትዮጵያ ተረካቢው ወገን እንዳለፈው ሁሉ ጥቂት ብልጣብልጦች የሥልጣን መወጣጫ እንዲሆናቸው በሚዘረጉለት ወጥመድ ውስጥ ገብቶ ዳግም ሰለባ እንዳይሆንና የተመቻቸ የጥፋት የጭድ ክምር በመሆን እነሱ በሚለኩሱት እሳትና በሚያርከፈክፉት ቤንዚን ሰደድና አቀጣጣይ እንደማይሆንላቸው ያለፈውን ሂደት ያጤኗል ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ በተካሄደው የከተማዋ አስተዳደር ምርጫ በሚገባ እውነተኛ የፖለቲካ ተዋናይነቱንና ሃገር ተረካቢነቱን በድርጊቱ ያረጋገጠበት ስለሆነ ከእንግዲህ ተላላነት ቀርቷል።

"የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል" ይላል የሃገርኛ ብሂላችን። መንግሥትና ሕዝብም የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎችን የቀቢፀ ተስፋ አፍራሽ እንቅስቃሴ በንቃት እና በዓይነ ቁራኛ እየተከታተሉ ዋና ትኩረታቸውን መጻኢው ምርጫ፣ አሁንም፣ ፍትሃዊ፣ ርትአዊ፣ ነጻና ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ ድባብን ተላብሶ እንዲደመደምና ሕዝቡ የሕገ መንግሥታዊ መብቱ ተቋዳሽ አንኳር ተዋናይና በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሕዝብ አዛዥና ናዛዥ ባለቤት መሆኑን ለማረጋገጥ በጽናት የመንቀሳቀስ ሃገራዊ፣ ትውልዳዊና፣ ሕገ መንግሥታዊ ግዴታቸውን ያለምንም እንከን መወጣት አለባቸው እላለሁ።

መንግሥትና ሕዝብ ይኸንን ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን በእውን፣ በምልዓትና በእርግጠኝነት ሲወጡ ነው የጥቂቶች የማስመሰል ትወና እርቃኑን ቀርቶ "የወረወርኩት አንካሴ ተመልሶ በራሴ " እንዲሉ ማንኛውም አደናቃፊ ሙከራቸው በሕዝብ ፊት ተጋልጦ ለማንነታቸው ተገቢውን ሕዝባዊ ብይን የሚያገኙት እላለሁ፣ በቸር ይግጠመን።